**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ**

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሸከርካሪ ጎማ የመቆለፍ አሠራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 47/2013

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ላይ እየታየ ያለውን የትራፊክ መጨናነቅ እና አደጋዎች ከሚያስከትሉ የተለያዩ ምክንያቶች መካከል ህገ-ወጥ በሆነ መልኩ መንገድ ላይ ያለ አግባብ ተሽከርካሪን ማቆም፣ ማሽከርከር በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ተሽከርካሪን ማሽከርከሪ እና ደህንነቱ ያልተጠበቀ ተሽከርካሪን ማሽከርከር የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 395/2009 ላይ የተዘረዘሩ የመንገድ ትራፊክ ጥፋቶች ተፈፅመው ሲገኙ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች በተመለከተ ዝርዝር የማስፈፀሚያ ስልቶች ባለመዘርጋታቸው በተለይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ባልያዙ፣ በቦታው ባልተገኙም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች አሽከርካሪዎች ላይ ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ግልፅ ባለመሆኑ የተሽከርካሪውን ሰሌዳ በመፍታት እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎችን መቀነስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀፅ 11 የትራፊክ ደንቦች መከበራቸውን ቁጥጥር እንዲያደርግ አግባብ ባለው ህግ ደንብ ተላላፊዎችን ላይ እርምጃ እንዲወስድና የማስፈፀሚያ ስልቶችን በመዘርጋት ተግባራዊነታቸውን እንዲያረጋግጥ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣

የተሽከርካሪጎማ የሚቆለፍበት አግባብ፣ የተሽከርካሪ ጎማ ሲቆለፍ ሊወሰድ የሚገባውን ጥንቃቄ እና የተቆለፈው የተሽከርካሪ ጎማ ሊከፈት የሚችልበት ሥርዓት እና ሌሎች ጉዳዮችን መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 3(ሠ) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አውጪው ባለስልጣን

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ የአዲስ አበባ አስተዳደር አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 3(ሠ) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ" **በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪ ጎማ የመቆለፍ አሠራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር** 47/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### 3. ትርጓሜ

1. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤
2. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. **"ተቆጣጣሪ መስሪያቤት"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት ስልጣን የተሰጣቸው በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ቁጥጥር እንዲሁም በሌሎች ህግ የማስከበር ተግባር ላይ የተሰማሩ መንግስታዊ ተቋማት ነው፡፡
4. **"ትራፊክ ተቆጣጣሪ"** ማለት የትራፊክ እና የትራንስፖርት ህጎችን ለማስፈጸም አግባብነት ባለው ህግ ስልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ወይም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ተብሎ ይታወቃል፣
5. **"ተሽከርካሪ"** ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚኔድ ማንኛውም ተሽከርካሪ ሲሆን ተሳቢና ግማሽ ተሳቢንም ይጨምራል፡፡
6. **"ባለሞተር ብስክሌት"** ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ100 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ከአራት መንኮራኩር በታች ያለው ባለ ሞተር ሽከርካሪ ነው፣
7. **"ትራፊክ"** ማለት በማንኛውም መንገድ አንድ ወይም ብዙ ሆነው የሚተላለፍ እግረኞች ወይም ሰው ተቀምጦባቸው ወይም እየተነዱ ወይም እየተጠበቁ የሚሄዱ እንስሶችና ተሽከርካዎች ናቸው፣

8. **"ግማሽ ተሣቢ"** ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለ ሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ የተሽከርካሪው ጭነትና ክብደት በከፊል በሌላ ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፣
9. **"እንስሳ"** ማለት ከውሻና ከድመት በቀር ማናቸውም የቤት እንሰሳ ነው፣
10. **"የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ"** ማለት የአደጋ አገልግሎት ተግባሩን ለመፈጸም በሚዘዋወርበት ወቅት በግንባሩ አቅጣጫ ሳያቋርጥ ብልጭ ብልጭ የሚል ቀይ ወይም ሰማያዊ የመብራት ምልክት የሚያሳይ ወይም ለማስጠንቀቂያ ተስማሚ የሆነ የድምፅ ምልክት ወይም ደወል የሚያሰማ አምቡላንስ፣የመከላከያ ወይም የፖሊስ ኃይል ወይም የእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከካሪ ነው፣
11. **"ነጠላ መንገድ"** ማለት በአንድ ረድፍ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን የሚያስኬድ በቂ ስፋት ያለው የመንገድ ክፍል ነው፣
12. **"ተሽከርካሪን በመዘግየት ማቆም"** ማለት ተሳፈሪዎችን ለማሳፈር ወይም ለማውረድ ወይም የንግድ ዕቃዎችን ለመጫን ወይም ለማራገፍ ከሚያስፈልገው ጊዜ በላይ ተሳፋሪ ወይም የንግድ ዕቃ በውስጡ ቢኖርም ባይኖርም የተሽከርካሪው መቆም ነው፣
13. **"እግረኛ ማቋረጫ"** ማለት እግረኞች አቋርጠው እንዲያልፉበት ተብሎ በመንገዱ ላይ የመንገድ ምልክት የተደረገበት የመንገድ ክፍልወይ ምድል ድይ ነው፣
14. **"የሐዲድ መንገድ ማቋረጫ"** ማለት መንገድና የሐዲድ መንገድ የሚገናኙበት መስቀለኛ መንገድ ነው፣
15. **"መስቀለኛ መንገድ"** ማለት ሁለት ወይም ከሁለት የበለጠ መንገዶች በመስቀለኛ መልክ የሚገናኙበት ሥፍራ ነው፣
16. **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 በደንብ ቁጥር 395/2009 እንደተሻሻለ ነው፡፡
17. **"መንገድ"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚገኝና በከተማ አስተዳደሩ የሚተዳደር ለማንኛውም ተላላፊ ትራፊክ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ዋና መንገድ፣ መለስተኛ መንገድ፣ መጋቢ.መንገድ፣ የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ የመንደርመንገድ፣ አደባባይ እና የአደባባይ ዙሪያ፣ የመንገድ አካፋይ ደሴት ነው፡፡

18. **“የእግረኛ መንገድ”** ማለት ተሽከርካሪዎች እንዲንቀሳቀስበት የተዘጋጀውን መንገድ ጠርዝ ተከትሎ ወይም ለብቻው ለእግረኛ እንቅስቃሴ የሚውል መንገድ ነው፡፡
19. **“የማብሪያ ጊዜ”** ማለት ከፀሐይ መጥለቂያ እስከ ፀሐይ መውጫ ድረስ ያለው ጊዜና እንዲሁ በአየር ሁኔታ ምክንያት ለማየት የማይቻልበት ወቅት ነው፣
20. **“የመንገድ ምልክት”** ማለት ተሽከርካሪዎች የሚተላለፍበትን አቅጣጫ ለመወሰንና እንዲሁም ለተላላፊዎች የሚያስጠነቅቅ፣ የሚከለክል፣ የሚያስገድድ፣ ቅድሚያ የሚያሰጥ እና መረጃ ለመስጠት የሚያገለግል ማንኛውም የመንገድ ምልክት ነው፣
21. **“የተሽከርካሪ ጎማ መቆለፊያ”** ማለት የመንገድ ትራፊክ ደንብ የተላለፈን ተሽከርካሪ በጊዜያዊነት እንዳይንቀሳቀስ ለማድረግ በተሽከርካሪዉ ጎማ ላይ የሚታሰር ቁልፍ ያለዉ ከብረት ከሌላ ቁስ የተሰራ መሣሪያ ነዉ፡፡
22. **“የተሽከርካሪ ጎማ መቆለፍ”** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሠረት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህጎችን በመተላለፍ የትራፊክ ፍሰቱ እና ደህንነቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደሩ ደንብ የተላለፈዉን ተሽከርካሪ ጎማ በጎማ መቆለፊያ ለጊዜው እንዳይንቀሳቀስ በማሰር የትራፊክ ደንብ ተላላፊው ላይ ህጋዊ የእርምት እርምጃ የመውሰድ ተግባር ነዉ፤
23. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ መንገዶችና የእግረኛ መንገዶች ላይ የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ህጎችን በሚጥሱ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 5. የጾታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ልዩ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ለሴትም ፆታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተሽከርካሪ ጎማ የሚቆለፍባቸዉ ሁኔታዎች

### 6. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ጥሰቶች

1. በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 እና በተሻሻለው ደንብ ቁጥር 395/2009 የተጠቀሱት የመንገድ ትራፊክ ደንብ ጥሰቶች በሚፈፀመበት ጊዜ ማንኛውም ተሽከርካሪ ጎማዉ ሊቆለፍ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀሻ ፈቃድ መመሪያ ለከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች በተከለከለ ሰአትና ቦታ ላይ ማቆምና በትራፊክ ተቆጣጣሪ እንዲነሳ ሲታዘዝ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በስፍራዉ ካልተገኘ ተሽከርካሪው ጎማው ሊቆለፍ ይችላል፡፡

### 7. የተሽከርካሪ ጎማ ለመቆለፍ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1. ከዚህ በታች የተጠቀሱ ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ የተሽከርካሪ ጎማ ሊቆለፍ አይችልም፡፡

   ሀ. ደንብ ተላላፊው አሽከርካሪ በአቅራቢያ የሌለና በቀላሉ ሊገኝ የማይችል ሲሆን፣

   ለ. አሽከርካሪው በአካል ተገኝቶ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፣

### 8. መመሪያው ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ተሽከርካሪዎች

በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) እና (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪን ጎማ መቆለፊያ መመሪያ በአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች እና በሌሎች ተመሳሳይ ተግባር ላይ የተሰማሩ ተሽከርካሪዎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም ፡፡

## ክፍል ሶስት
## ተግባርና ኃላፊነት

### 9. የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት

1. ማንኛዉም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የተሽከርካሪን ጎማ ለመቆለፍ ከመሰማራቱ በፊት ስለ ስራዉ ተገቢውን ስልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለባቸው፡፡
2. የሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ መስሪያቶች የትራፊክ ተቆጣጣሪው ለስራ የሚያስፈልገውን መሳሪያዎችና ግብአቶች የማሟላት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### 10.ከትራፊክ ተቆጣጣሪ የሚጠበቅ ኃላፊነት

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሠረት የትራፊክ ተቆጣጣሪ ተሽከርካሪው ጎማ ከመቆለፉ በፊት እና በኃላ ተሽከርካሪዉ የቆመበትን ቦታና ሁኔታ በተመለከተ በቂ መረጃ መያዝ አለበት፤
2. የትራፊክ ተቆጣጣሪዉ ጎማዉ የተቆለፈበት ተሽከርካሪ ላይ በቂ ማስታወሻ ወይም መረጃ የያዘ ስቲከር በአሽከርካሪው መግቢያ በር መክፈቻ እጀታ ላይ መለጠፍ አለበት፤
3. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ ጎማው የተቆለፈበትን ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ወይም ባለንብረት ወይም ህጋዊ ተወካይ ወደ ትራፊክ መቆጣጠሪያ ዋና ክፍል /መምሪያ/ ወይም ኤጀንሲው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ እና በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ የተጠቀሰውን ማስታወሻ ይዞ ከቀረበ ባጠፋው የጥፋት እርከን መሰረት የደንብ ተላላፊ ትኬት መስጠት አለበት፤
4. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ ወደ መስክ ወይም የደንብ መስከበር ታግባር ከመሰማራቱ በፊት ማንነቱን የሚገልጽ የመስሪያቱ መታወቂያ፣ ባጅ፤ ለሥራዉ የተዘጋጀ የደንብ ልብስ፣ መገነኛ ሬድዮ እንደሁኔታው፣ የጎማ መቆለፊያ ከነ ሙሉቁሳቁስእንዲሁም የቅጣት ፓድ መያዝ አለበት፤
5. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የደንብ ተላለፊን ተሽከርካሪ ጎማ ከመቆለፉ በፊት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተገለጹትን ግልጽ የሆነ የመንገድ ትራፊክ ደንብ ጥሰት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፤

6. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የተሽከርካሪን ጎማ ከመቆለፉ በፊት በሌላ አማራጭ የመንገድ ትራፊክ ደንብ ጥሰት ላይ እርምጃ ለመውሰድ የማይቻል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤
7. ማንኛውም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ሲያስፈፅም ከአድሎ በፀዳ ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፤
8. የትራፊክ ቁጥጥር ተግባሩን ሲያከናውን ለደንብ ተላላፊዎች ሙያው የሚጠይቀውን ተገቢውን አክብሮት ያላሳየ፣ ያመናጨቀ ወይም የተሳደበ በማናቸውም ምክንያት አድሎ የፈፀመ ወይም ጥፋተኛ ያልሆነ አሽከርካሪን ተሽከርካሪ የቆለፈ እንደሆነ አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቅ ይደረጋል፤

## 11.ስለደንብ ተላላፊ ኃላፊነት

1. ማንኛውም የተሽከርካሪው ጎማ የተቆለፈበት አሽከርካሪ ወይም ባለንብረት ወይም ህጋዊ ተወካይ ባጠፋዉ የጥፋት እርከን መሰረት የመንገድ ትራፊክ ደንብ ተላላፊዎች የቅጣት ትኬት ከፍሎ ደረሰኙን መያዝ አለበት፡፡
2. መንኛውም የተሽከርካሪዉ ጎማ የተቆለፈበት አሽከርካሪ ወይም ባለንብረት ወይም ህጋዊ ተወካይ ጎማዉ የተቆለፈበትን ተሽከርካሪ ለማስከፈት ወደ ኤጀንሲዉ ወይም ወደ ትራፊክ ተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት በሚመጣበት ወቅት ከላይ የተጠቀሰውን ቅጣት የከፈለበትን ደረሰኝ እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀፅ (2) ላይ የተጠቀሰውን ማስታወሻ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡
3. ደንብ የተላለፈው አሽከርካሪ በራሱ ጊዜ የተሽከርካሪ ጎማ መቆለፊያውን ለመክፈት በመሞከሩ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በጎማ መቆለፊያው ላይ ጉዳት ካደረሰ በወንጀል ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ለደረሰው የንብረት ጉዳት በወቅቱ ዋጋ የጎማ መቆለፊውን ግምት እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት በጎማ መቆለፊያው ላይ ጉዳት በማድረሱ ግምቱን እንዲከፍል ኃላፊነት ያለበት አሽከርካሪ ግምቱን እስኪከፍል ድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ በትራፊክ ተቆጣጠሪው ስር እንዲሆን ይደረጋል፡፡

5. ደንብ ተላላፊው አሽከርካሪ የተሽከርካሪው ጎማ በትራፊክ ተቆጣጣሪው እንዳይቆለፍ ያደረገ እንደሆነ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስትን ስራ በማደናቀፍ ወንጀል እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡
6. ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ጎማው የተቆለፈበት ሰው ቅሬታ አቅርቦ ቅጣቱን ካላሻረ በስተቀር የተጣለበትን ቅጣት በ10 የስራ ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት፡፡
7. ቅጣቱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (6) በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ያልከፈለ አሽከርካሪ ተጨማሪ ቅጣትና የጥፋት ሪከርድ ይያዝበታል፡፡

## 12.ጎማቸው በተቆለፈባቸው ተሽከርካሪዎች የሚለጠፍ መረጃ ይዘት

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ጎማቸው በተቆለፈባቸው ተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፉው መረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ነጥቦችን የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

   ሀ. የተቆለፈበት ምክንያት፤

   ለ. ቀን፣ ሰዓትና ፣

   ሐ. የተሽከርካሪው አይነት ፤

   መ. የጥፋቱ ዓይነት (እርከን)

   ሠ. የተቆጣጣሪዉ ስምና ፊርማ፤

   ረ. የኤጀንሲዉ ወይም የፖሊስ ጽህፈት ቤት ሙሉ አድራሻ፤

## 13.የጎማ መቆለፊያ ቁልፍ ገቢ ስለማድረግ

ማንኛዉም የትራፊክ ተቆጣጣሪ የተሽከርካሪዉን ጎማ ከቆለፈ በኃላ የተሽከርካሪ ጎማ የተቆለፈበትን ቁልፍ ወድያውኑ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የቅጣት ኦፊሰር ማስረከብ አለበት፡፡

## 14.ተገቢ ጥንቃቄ ስለ ማድረግ

1. የተሽከርካሪ ጎማ መቆለፍ ተግባር የሚያከናዉን የትራፊክ ተቆጣጣሪ የተሽከርካሪዉን ጎማ በሚቆልፍበት ወቅት ተሽከርካሪዉ ላይ እና በራሱ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፤
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ  አንቀፅ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የመንገድ ትራፊክ ደንብ በመተላለፍ የተሽከርካሪው ጎማ በተቆለፈበት ተሽከርካሪ ለሚደርስ ማንኛውም አይነት ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ አደጋ፣ ጉዳት ወይም ስርቆት ጎማው እንዲቆለፍ ያደረገው የትራፊክ ተቆጣጣሪም ሆነ የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡

## ክፍል አራት
## ጎማው የተቆለፈበትን ተሽከርካሪ ስለመክፈት

## 15.የተቆለፈውን የተሽከርካሪ ጎማ ስለመክፈት

1. ደንብ ተላላፊው የተሽከርካሪው ጎማ ከተቆለፈ በኃላ የትራፊክ ተቆጣጣሪው ከአካባቢው ሳይቅ ደርሶ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ለተቆጣጠሪው ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ የክስ ቻርጅ ከተሰጠው በኃላ የተሽከርካሪው ጎማ ወድያውኑ ይከፈትለታል፡፡
2. ማንኛውም የተሽከርካሪዉ ጎማ የተቆለፈበት አሽከርካሪ ወይም ባለንብረት ወይም ህጋዊ ተወካይ ጎማዉ የተቆለፈበትን ተሽከርካሪ ለማስለቀቅ ወደ ኤጀንሲዉ ወይም ወደ ትራፊክ መቆጣጠሪያ ዋና ክፍል (መምሪያ) የከፈለበትን የቅጣት ደራሰኝ ይዞ ሲቀርብ የተቆለፈበት የተሽከርካሪው ጎማ እንዲከፈትለት ይደረጋል፡፡

## 16.ተሽከርካሪን ከመንገድ ስለማስነሳት

1. የመንገድ ትራፊክ ደንብ በመተላለፉ ምክንያት ጎማዉ የተቆለፈበት ተሽከርካሪ አሽከርካሪዉ ወይም ባለንብረት ወይም ህጋዊ ተወካይ ለከባድ ተሽከርካሪ በሶስት(3) ሰዓት ውስጥ እንዲሁም ለቀላልና መለስተኛ ተሽከርካሪ በሁለት/2/ ሰዓት ውስጥ በትራፊክ ተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት ፊት ቀርቦ ግዴታውን በመወጣት የተሽከርካሪው ጎማ እንዲከፈት ካላስደረገ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተሽከርካሪ

ከመንገድ ሊነሳ የሚችልበት አሠራርን ለመወሰን በወጣ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪው በክሬን ከመንገድ እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

2. ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተሽከርካሪ ከመንገድ ሊነሳ የሚችልበት አሠራር ለመወሰን በወጣ መመሪያ መሠረት ተሽከርካሪ ከመንገድ እንዳይነሳ ሊገድብ አይችልም፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለ ቅሬታ አፈታት

### 17.ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1. በዚህ መመሪያ መሠረት በትራፊክ ተቆጣጣሪው የተሰጠዉ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በፅሁፍ ለትራፊክ ተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት በሁለት ቀን ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቅሬታው በቀረበ በአምስት የሥራ ቀን ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
3. የትራፊክ ተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት የትራፊክ ተቆጣጣሪውን ውሳኔ ካፀደቀው ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት በአምስት የሥራ ቀን ውስጥ ውሳኔ መስጠት ካልቻለ ቅሬታ አቅራቢዉ አካል ቅሬታውን ለቢሮው በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ቢሮው ቅሬታው በቀረበ በአሥር የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
5. የቢሮው ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18.የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

## 19.ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች

በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚቃረን መመሪያም ሆነ የተለመደ የአሰራር ልምድ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

## 20.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

ይህ መመሪያ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በጅምር ወይም በሂደት ላይ ያሉ መመሪያዉን የሚመለከቱ ጉዳዮች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

## 21.መመሪያ ስለማሻሻል

ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ይህን የአፈጻጸም መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 22.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 22 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መጋቢት 22 ቀን 2012 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**ኢንጅነር ጅሬኛ ሂርጳ ደበሎ**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ**

**ዋና ዳይሬክተር**